# ኩርኩም?

በላይ ተሰማ

ኢትዮጵያን የሚያክል ሃገርን ወክሎ
ለዕጣ ፈንታዋ ሕዝብን ኣሥቀድሞ
ቀረና ድርድር በጥብቅና ቆሞ
ጭራሹን ሊያሣርድ የንግልል ኣጋድሞ
እጅ የሚሰጥ መሪ በነጭ ተኮርኩሞ
በሥተ እርጅና ውርደት !
ከመቃብር ኣፋፍ ባንድ እግር ተንጠልጥሎ ።

ኤሎሄ ኢሎሄ እግዜኦ መሃረና
ብዩ ኣሁንሥ ልጩህ ቅሌት በዝቷልና
ሽንፈትና ውርደት እጅ እጅ ኣለኝና
ዓይኔም ደካከመ ፤ ጉልበቴም እራደ ሃይሉ ተረታና።

ክህደቱን ዓላማው ኩርክምን መመሪያው
ሽራተንን ማዕከል ኣርጎት የትግል ኣምባው
በምርኩዝ እሩጦ በኩርክም ተገጭቶ
ትግሉን ሣቢ መጣ የኋሊት ጎትቶ
ለጌታው ታማኙ ኣጎንባሽ ተመርጦ ።

ይሄ ሁሉ ድግሥ ይህ ሁሉ ጫጫታ
ለሆዳቸው ብለው ለሥልጣን ሽርፍታ
ኮርኩመው ቢያሥገቡት ከበርጩማው ጌታ
ኣገር ወዳድ ጀግናው የሕዝቡ ኣለኝታ
ከቶ እንዳይመሥላችሁ ትጥቁን የሚፈታ
ኣዳምጡኝ በነከናቸ የታሪክ ቅርሻታ
ጥምረታችሁ ትብያ ሲሆን ታዩኝ ማታ !!

11/12/09.

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.